## የሀላባ ልዩ ወረዳ አቅም ግንባታ ጽ/ቤ

# የ2002 በጀት ዓመት የስራ ዕቅድ

ሰኔ 2001 ዓ.ም

ቁሊቶ

# መግቢያ

በልዩ ወረዳችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት ከልማቱም ህዝቡም በበቂ ደረጃ ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል መልካም አስተዳደር የሠፈነበት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት ወሳኝ ነው ፡፡ ስለሆነም መሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግባራን በአዲስ አሠራር አደረጃጀትና በበቃ የሰው ሀብት ልማትና አመራር በመታገዝ በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በማፋጠን በማቀላጠፍ ተቋማዊ ለውጥ እውን ማድረግ እና መልካም አስተዳደርን እያሰየ መምጣት እንዲያስችል የጽ/ቤቱ 2002 በጀት አመት ቁልፍ የትኩረት መስክ ሆኖ ተጽፏል ፡፡

በዚህም መሠረት በየደረጃው የሚታዩትን የማስፈፃሚያ አቅም ጉዳዮችን ደረጃ በደረጃ ለመፍታት ፈጣን ስልት በመቀየስ በተግባር ላይ እንዲውል በማድረግ እና የሪፎርም ስራዎችን በተጠናከረ መልኩ ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል ፡፡

በአጠቃላይ የ2002 በጀት አመት እቅድ በዋናነት የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ስርዓት ማስፈን በመንግሥት ተቋመት ቁልፍና ውጤታማ አሠራር መዘረጋትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በዙህም መሠረት የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ስትራቴጂያዊ ግቦች በዋናነት በመውሰድ የ2002 በጀት አመት እቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

# 1. ዓላማ

የመንግስት ተቋማትን የማስፈፀሚያ አቅም በመገንባት ፍጣንና ቀጣይነት ያለው ለማት በማረጋገጥ በመልካም አስተዳደር እምርታ ማምጣት ነው ::

# 2. የጽ/ቤቱ ቁልፍ አብይና ንዑስ የትኩረት መስኮች

## 2.1 ቁልፍ የትኩረት መስክ

- የመሠራታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ትግባሩን በአዳዲስ አሠራር አደረጃጀትና በበቂ የሠው ሀብት ልማት አመራር በመታገዝ በዘመናዊ እንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ በማሠለጠንና በማቀስጠፍ ተቋማዊ ለውጥን እውን ማድረግ እና በመልካም አስተዳደር እምርታ ማምጣት::

## 2.2 ዓብይ የትኩረት መስኮች

- ተቋማዊ የማስፈፃሚያ አቅም ክፍተቶችን ለመሙላት የሚደረጉ ጥሬቶችን ተግባራዊ ማድረግ
- በጽ/ቤቱ የሚከናወኑ ተግባራትን በመጽሄት በማጀብ ለህዝቡ ወቅታዊ መረጃ እንዲደርስ ማድረግ::
- በልዩ ወረዳው አመራር በስርዓት ፆታና ኤች ቪ ኤድስ እንቅድቃሴ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሠሩና የመሪነት ሚና እንዲጫወት ማድረግ::

# 3. የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት ግቦች

## 3.1 በቁልፍ የትኩረት መስኮች

---

3.1.1. የመሠራታዊ የስራ ሂደት ለውጥን የተሟላ ለማድረግ ከክልሉ ተጠንተው በሚወርዱ የጥናት ውጤቶች ከልዩ ወረዳው ሁኔታ ጋር በማስማማት የተዘረጋና ስራ ላይ የዋለ አሰራር

3.1.2 በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተተገበረ የመሠራታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ( BPR )

3.1.3 በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረጋ ሚዛናዊ ውጤት ተኮር እቅድ አዘገጃጀትና አሠራር

3.1.4. በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረጋና ስራ ላይ የዋለ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሠራር

- በሁሉም ቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ተግባራዊ ለማድረግ የተዘረጋና ስራ ላይ የዋለ የኢንስፔክሽን አደረጃጀትና አሠራር

3.1.5. በሁሉም ቀበሌ መዋቅር በግንባር ቀደም አርሶ አደር እንዲማር ማድረግና አሳምኖ ማሰራትን በመጠናከር ምርጥ ተሞክሮዎችን ማስፋፋት

3.1.6. በሁሉም ቀበሌያት የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ ተቋማት መዋቅር የተዘረጋ አሠራርና አደረጃጀት ስርዓት

3.1.7. በሁሉም ቀበሌያት የተዘረጋና ስራ ላይ የዋለ የኮሚኒቲ ፖሉሲንግ የአመራር የሙግት መፍቻ ስርዓት

3.1.8. በልዩ ወረዳው ባሉ የፍትህ ተቋማት የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አስተባባርን ተደራሽ ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ የተደረገ ድጋፍዊ ክትትል

3.1.9. በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች የአፈፃፀም ስልቶችና ጉዳቶች ላይ የተደረገ ጥራት

3.1.10. በልዩ ወረዳው የተስፋፋ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ መሠረተ ልማት ማህበረሰብ መረጃ ማዕከልና ወረዳኔት

3.1.11 ሰው ሀብት ልማትና ስልጠና አቅሙ የጎለበተ የወረዳው የከተማ አስተዳደር አመራር እና ባለሙያ

3.1.12 ልዩ ወረዳው የሰው ሀብት ስራ አመራር በስራ ጉዳይ የሚገኙትን የአሠራር ስርዓቶች ስራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የተሠጠ ስልጠናና የምክር አገልግሎት

## 3.2 *አብይ የትኩረት መስኮች*

*ግቦች*

3.2.1. በልዩ ወረዳው የተቀናጀ የእቅድ አዘገጃጀት የሪፖርት አቀራረብና የጽ/ቤቱ የረዥምጊዜ እቅድ

3.2.2. በተጠናከረ መንገድ የተተገበረ የስርዓት ጾታና ኤች አይ ቪ ኤድስ ስትራቴጂ

3.2.3. ለህ/ሰቡና ለተጠቃሚዎች የተሰራጩ የጽ/ቤቱ ወቅታዊ መረጃዎች

# 4. *የጽ/ቤቱ ግቦችና የሚጠበቁ ውጤቶች*

## 4.1 *ቁልፍ የትኩረት መስክ*

4.1.1. መሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥን የተሟላ ለማድረግ ከክልል ተጠንተው የሚመጡ የጥናት ውጤቶች ከልዩ ወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረጉና ስራ ላይ የዋሉ አሠራሮች

- ከBPR ጋር የተጣጣመ የሽግሽግ የስራ ምዘናና ደረጃ አሠጣጥ ስርዓት
- በውጤት ተኮር ላይ የተመሠረተ የልማት ስርዓት
- ከኃላፊነት የሚነሱ ተሸሞዎች ጥቅማ ጥቅም ለማስጠበቅ የተዘረጋ ስርዓት

4.1.2 በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የተተገበረ መሰረታዊ የስራ ለውጥ (BPR)

- የሁለተኛ ዙር BPR ለሚተገበሩ የሴክተር ሠራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ለሙሉ ትግባራ የተሰጠ ስልጠና
- በሁሉም የመንግስት ተቋማት ለመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ለመተግበር የተደረገ የክትትል ድጋፍ

4.1.3 በመንግስት ተቋማት ሚዛናዊ ውጤት ተኮር ማስፈፀሚያ ማንዋል

- ታትሞ የተሠራው የውጤት ተኮር ማስፈፀሚያ ማንዋል
- በውጤት ተኮር የዕቅድ አፈጻጸም ስርአት ላይ የሰለጠኑ አመራሮችና ባለሙያዎች
- በጽ/ቤቶች የተደረገ የውጤት ተኮር እቅድ አተገባበር ድጋፋዊ ክትትል

4.1.4. በልዩ ወረዳው የተስፋፋ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ማህበረሰብ መረጃ ማእከልና ወረዳ ኔት እንዲሁም ስኩል ኔት

- በልዩ ወረዳው እና በከተማ የተበላሹ የ ICT መሳሪያዎችን ቀላልና መለስተኛ ጥገና ማከናወን
- በከተማ አስተዳደር ያለውን የግብር አሰባሰብ ስራ ለማቀላጠፍ የሚያስችል ስርአት መዘርጋት

በወረዳው የተቋቋመውን መረጃ ማእከል መከታተል

የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ማስፋፋትና በዘርፉ የሰለጠኑ የሰው ሀይል ለማፍራት የተሰጠ ስልጠና

- በመሰረታዊ የኮምፒውተር አጠቃቀም የተሰጠ ስልጠና
- በኢንተርኔት ኢሜል አጠቃቀም የተሰጠ ስልጠና
- በቪዲዮ ኮንፈረንሲንግ የተደረገ የልምድ ልውውጥ
- በወረዳ የ------------------- ለማጠናከር የሚደረጉ ፓናል ውይይቶች

4.1.5. በዘመናዊ መረጃ አያያዝ የሰለጠኑ የመንግስት ሰራተኞች

- ወቅቱን ጠብቀውና በአግባቡ ተደራጅተው የተቀመጡ በሰው ሀይል መረጃዎች
- ለተገልጋዮች የተሰጡ መረጃዎች

4.1.6. ሠች ፐርሰንት የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈጻጸም ችግሮችን፣ቅሬታዎችና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች

- ለቀረበ ቅሬታ ተጣርቶ የተሰጠ ውሳኔ
- ለቀረበ ቅሬታ በስፍራው ተገኝተው የተጣሩና የተሰጠ ውሳኔ
- የተፈጸሙ ቅሬታ ወሳኔዎች
- በሰው ሀብት ስራ አመራርና አፈጻጸም ክፍተት መነሻ ለቀረቡ የደግባኝ ጉዳይ ዉሳኔ መስጠት

4.1.7. በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረጋ ስራ ላይ የዋለ የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበት አሰራር

- የተገልጋዩን ቅሬታ ለመፍታት የተዘጋጀና የተተገበረ የተቋም ቻርተር

4.1.8. የሰው ሃብት ልማት በስልጠና አቅሙ የጎለበተ የወረዳ የከተማና የቀበሌ አመራርና በሰሙያ እንዲሁም ለመንግስት ሰራተኞች በመንግስት ፖሊሲ ከመሰረታዊ የስራ ሂደት ጽንሰ ሃሰብ ላይ የተሰጠ ስልጠና

4.1.9. በሰው ሀይል ልማት ስትራቴጂና መመሪያ የተሰጠ ስልጠና

4.1.10. ሴክተር መስርያ ቤቶችን የተገልጋዩን ፍላጎት መሰረት አድርጎ የተሰጠ ስልጠና

## 4.2 አብይ የትኩረት መስኮች

4.2.1. በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ የህ/ሰቡና ለተጠቃሚዮዎች የተሰራጩ የጽ/ቤቱ ወቅታዊ መረጃ

4.2.2 ተቋማዊ የማስፈጸጸሚያ አቅም ክፍተቶች ለመሙላት የተደረጉ ጥናቶች

- የተዘጋጀ የሰው ሀይል ልማት ስትራቴጂዎች
- የተካሄደ የስልጠና ፍላጎት
- የተሸሻለ  የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የትምህርት ዕድል የአፈጻጸም መመሪያ
- የተገልጋዮች እርካታ መረጃ መለኪያ ጥናት

# 5. አመታዊ ግቦች ውጤት ስኬትና ፋይዳ አመልካቾች

| ተ.ቁ | የትኩረት መስኮችና ሴክተሪያል ግቦች | የውጠት አመልከቾች<br>Out put indicators | የግብ ስኬት አመልከችች<br>Out put indicators | ፋይዲ አመልከችች<br>impacts |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ቁልፍ የትኩረት መስክ | መሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ሀብት ልማትና አመራር ቀልጣፋና ተቋማዊ ለውጥ | ትግባራ በአዲስ አሠራር በመተገዝ ዘመናዊ ኢንፎርሚሽን ቴክኖሎጂ እውን ማድረግና<br>በመልካም አስተዳደር | በበቂ የሰው እርምታ ማምጠት |
| 1 | የመሠራታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የተሟለ ለማድረግ ከክልል የሚወርዱ የጥናት ውጤቶች ከወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጠም የተዘረጋ | የተዘገጃ ጥናት ውዩቶች ብዘት | የተአረገ የአሰራር ስርዓት | የተፋጠና የማህባራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማት |
| 2 | በሁልም መንግስት ተቋማት የተጠናከረ ድጋፍና ክትትል በማድረግ የትግባራ መሠራታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (BPR) | የተዘገጀ ጥገና ውጤቶች ብዘት | የተአረገ የአሠራር ስርዓት | |
| 3 | ሁሉም መንግስት ተቋማት ሚዛናዊ ውጤት ተኮር እቅድ | BPR ስርዓት የተገበሩ መ/ቤቶች | ቀልጠፋና አገልግሎት መስጠት የቻሉ ተቋማት የተገልገዩች እርካታ በማባረታቸ ስርዓት ሠራተኞቻቸውን ያነሣሱ ተቋማት | |
| 4 | በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተዘረገ ስራ ላይ የዋለ የተገልጋዩች ቅሬታ የሚያስተናገድበትአሰራር መዘርጋት | የተገልገዩች ቅሬታ የሚስተናገድበት ስርዓት የተዘረጉ መ/ቤቶች | የደንነኞች እርካታ | |
| 5 | በወረዳና በቀበሌ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ ትግባራ ለማድረግ የተዘረጋና ስራ ላይ የዋለ የኢንስፔክሽን አደረጃጀትና አሠራር ማጣናከር | ኢንፔክሽን ቡዱን አባለት የተቋቋማባቸውና ቀበሌዎች ብዛት<br>ለኢንስፔክሽን አሠራር የተዛጋጃ ሰነድ<br>ኢንስፔክሽን የወሰዱ አባላት ብዛት<br>የኢንስፔክሽን አገልግሎት የተሰጣባቸው ተጣሪዎች<br>አሠራሩን ለማጠናከር የተሰጠ ድጋፋዊክትትል | ኢንፔክሽን ስራዎችን ተግባራዊ ያደረጉ ቡዱኖች በስልጠናው የረኩ<br>የኢንስፔክሽን ቡዱን አባላት<br>በወረዳውና በቀበሌ መካካል የተፈጠረ ግንኙነት<br>ተቋማዊ አሰራራቸውውን ያስተካከሉ ቀበሌዎች ብዛት | በግልፅነት ተጠያቂነት አሰራረ ላይ ለውጥ ያመጡ ወረዳና ቀበሌዎች የተፋጠና የቀበሌ ልማትና ህዝብ ተሠትፎ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6 | በሁሉም የልዩ ወረዳ ቀበሌ መዋቅር በግንባር ቀደም አርሶ አደር እንዲመረ ማድረግና አሣምኖ ማሠራትን በመጠናከር የምርጥ ተግባሮችን ማስፋፋት | በመልስና በግል ስራ ላይ በተገቢው የህ/ሰብ ተሣትፎን ለማረገጋጥ የተፈጠረ አሰራር ለምርጥ ተሞክሮ የተዛገጁ ቀበሌዎች መርሴል ለመፍጠር እና ለመመረጥ የተፈጠረ አሰራር | በማህባራሰብ ውስጥ የተፈጠሩ የልማት ተነሣሽነት ሞዴል አመራር ላይ የህ/ሰቡ እርካታ የህ/ሰብ ተሣትፎ መጠን | የዲሞክራሲ አሠራር መግባበት በገጠር ቀበሌ የልማታዊ ፖለቲከዊ ኢኮኖሚ አስተሰሳብ መደባር |
| 7 | በሁሉም ቀበሌያት ሥራ አስከያጅ በተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እንዲሠሩ የተዘረጋ የአሠራርና የአዳረጃጀጃት ስርዓት መዛረጋት | ስልጠና የተሰጣቸው ስራ አስከያጆች ብዛት<br>ተቋማዊ አሠራር የዘረጉ ቀበሌያት ብዛት | በቀበሌው ልማት ውስጥ የተፈጠሩ ተነሣሽነት በቀበሌ ህ/ሰቡን እርካታ ያደረጉ ተሣትፎ | በግልፅነት እና ተጠያቂነት አሠራር ላይ ለውጥ ያመጡ ወረዳዎችና ቀበሌዎች |
| 8 | በሁሉም ቀበሌያት የተዘረጉ ስራ ላይ የዋለ የኮሚኒቲ ፖሊስንግና አመራጭ የሙግት መፍቻ ስርዓት ማዘረጋት | ኮሚኒቲ ፖሊስንግ አዳረጀጃት የተቋቋማላቸው ቀበሌዎች ብዛት በስልጠናው የረኩ ሰልጠኞች ብዛት ስልጠና የወሰዱ አካላት ብዛት | የአካባቢ ሰላምና ጸጥታ መጠባቅ የቻሉ ቀበሌያት | የተፈጠሩ ማህባራዊና የኢኮኖሚ ልማት |
| 9 | በሁሉም የፍትህ ተቋማት የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበር ተደራሽ ውጤታማ ቀልጠፋ ለማድረግ ድጋፋዊ ክትትል | ድጋፋዊ ክትትል የተደረገላቸው የፍትህ ተቋማት | ተደራሽ ውጤታማ ቀልጠፋ አገልግሎት መስጠት የቻሉ የፍትህ | የተፈጠነ ማህባራዊ ኢኮኖሚ ላማት |
| 10 | አቅም ህንባታ ፕሮግራም የአፋፃፀም ስኬቶችና ጉዳዩች ላይ የተደረገ የፈይድ ጥናት | የአፈፃፀም ስኬቶች ጉድለቶች ላይ የተደረገ የፋይዳ ጥናት ብዛት | ለቀጣይ አቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ላይ የተቀመጣ ግንኙነት | የተፈጠረ ማህባራዊ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት |
| 11 | በወረዳው የተዘረገና የተስፋፋ የኢንፎርሜሽን መሠረተ ላማት ማህባረሳብ መረጃ ማዕካል ወረዳኔት በእኩልነት ማጠናከር | የተዘረጋ የኔትወርክ በኔትወርክ አኢንፎርሜሽን ላይ የተሰጠ ስልጠና ዘመናዊ ቴክኖሎጅ መረጃ መጣቀሚያ የጀመሩ ተቋማት ብዛት<br>የፕላዝማ ት/ርት ያገኙ ት/ርት ቤቶች | የተፈጠና መረጃ አገልግሎት መስጠት ግልፅ አሰራር መፍጠር የት/ርት ጥናት መጨመር | የተፋጣና የማህባራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት የመስፈፀም እና የማስገነባት ሴ/መ/ቤቶች |
| 12 | አስቀጣይ ተቋማት የማስፈፀም አቅም ለማሰደግ የተፈጠረ አቅም ግንባታ ስልጠና | በተለያዩ የስልጠና መስኮች አቅም የተገነባቸው አስቀጣይ ተቋማት ባላሙያዎች ብዛት በአቲ ቴክኖሎጅ መሠረት ልማት የተዘረጋላቸው | ሠልጥነው ስራ መተርጎም እና ማሣልጠን የቻሉ ባላሙያዎች የስራ ሂደቱን ቅልጥፍና መጨመር በተሰጣቸው ስልጠና ውስጥ አሰራረቸውን ያሻሻሉ ተቋማት | በስልጠና ለውጥ ቀልጠፋ አገልግሎት አሰራር ስርዓት መፍጠር ስራ ፈጠን መደበሩ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 13 | 100 % በዘመናዊ መረጃ አያያዝ የተደረጃ የመንግስት ሠራተኞች አጣቃላይ መረጃ | የሰው ሀብት ሀይላቸውን በዘመናዊ የረጃ አያያዝ ያጠናከሩ መ/ቤቶች ብዛት | ከውሳኔ አሠጠጥ አመቺ የሆነ የሰው ሀይል መረጃ | ለልማት አጋዥ የሆነ የሰው ሀይል መፍጠር |
| 14 | 100 % የተፈቱ አስተዳደራዊ የአፈፃፀም ችግሮች ቅሬታዎች እና ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች | ለይግባኝ የተሰጠ ውሳኔ<br>ለቅሬታ የተሰጠ ውሣኔ የአጋልገይ እርካታ መለኪያ ጥናት<br>ለፈፃሚዎች የተደረገ ድጋፋዊና ክትትል | የተፈጠረ መልከም የስራ ግንኙነት የተገልጋይ እርካታ | ለልማት የሆነ ሀይል ፍትሃዊ ምላሽ እያደረገ መምጠት |
| 15 | በሰው ሀብት ላማትና አውሙ የጎለበተ የሰው እና የከተማ የቀበሌ አመራር እና ባለሙያ | የሠለጠኑ የአመራርና ባላሙያ አካላት ብዛት በት/ርት አቅማቸው የጎለበተ ሠራተኞች ብዛት ፍላጎታቸው የረኩ መስሪያ ቤቶች የሀገር ውስጥ የት/ት የተከታተሉ ሠራተኞች ብዛት | ሰልጥነው በስራ መተርጎም የቻለ አመራር አካላት ባሙያ በተሰጠው ስልጠና መሠረት መተግባር የቻሉ የቀበሌ ስራ አስከያጆች በስልጠና ዕል አግኝተው የተማሩ ሠራተኞች በልዩ | ወረዳ ማ/ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ የመጣ ለውጥ |
| 16 | በወረዳው የሰው ሀብት ስራ አመራር ላይ የሚገኙትንና አዳዲስ የአሰራር ስራዓቶችን ስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ የተሰጠ ስልጠናና የምክር አገልግሎት | በአዳዲስ አሠራሮች ላይ የተሠጠ ስልጠና በስልጠናው የረኩ ተገልጋዩች ግንዘቤ የተፈጠረላቸው መ/ቤቶች | በስራ ላይ የዋለ አደዲስ አሰራሮች የበቁ ተገልጋዩች | ቀልጠፋና የአገልግሎት አሰጠጥ ስርዓት መፍጠር የተገኘ የአስተሣሰብ እና የአሠራር ለውጥ የስራ ተነሳሽነት እንዲኖር ማድረግ |
| 17 | በጽ/ቤቱ የተፈጠረና በተጠናከረ መንገድ የተተገባረ የስርዓተ ፆተና ኤች አይ ቨ ኤድስ ሰትራቴጂ | የስርዓት ፆታና ፀረ-ኤች አይ ቪ ኤድስ ሰትራቴጂ ላይ የተፈጠረ ግንዘቤ | ጤናማ እረሱን የጠበቀ ከኤኤች አይ ቪ የጠበቀ ባላሙች አመራሮች | ጤናማ አመራሮች ስታፍ |
| 18 | ሰላማዊ የማስፈፀም አቅም ክፍታቶች ለመሙለት የተደረጉ ጥናቶች | የተካሄዳ ጥናት የተዘገጃ ሙጂሊች ብዛት<br>የተዛጋጀ የሰው ሀይል መጠንና ሰትራቴጂ ሰነድ<br>የተዘገጀ የስልጠና መመሪያ | በተደረገው ጥነት የተለያዩ ስልጠና ክፍሎች<br>ስልጠና ለመስጠት ዶክመንት የተዘጋጀ ዝግጅት እና አሠራር ያስተከከሉ ተቋማት ሀገር ውስጥንና የወጭ ሀገር ስልጠና መመሪያ | በሰጠው ስልጠና የተገኘ ተቋማዊ<br>ለውጥ<br>ሰትራቴጂውን ለመተገባር የመጣ ለውጥ የተፈጠረ ፍትሀዊ የሰው ጠና ስርዓት |

# 6. *አዎንታዊና አሉታዊ ታሳቢዎች*

## 6.1.አዎንታዊ ታሳቢዎች

- የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያና የአገልግሎት ለውጥ ማድረግ

የሰራተኞችን ግንዛቤ ማዳበርና በግቦች ላይ የጋራ መግባባት መፍጠር

- መሰረታዊ የስራ ሂደትን ለውጥ ወደተሟላ ትግበራ ማስገባት
- የተጠያቂነትንና ግልጸኝነረት አሰራር እያሰፈኑ ማምጣት

## 6.2. አሉታዊ ታሳቢዎች

- የጽ/ቤቱ መደበኛ በጀት ማነስ
- የተሸከርካሪ ተሟልቶ አለመገኘት
- በአቅም ግንባታ ፕሮግራሚች ላይ በደረጃ የሚገኙ አመራሮችን ግንዛቤ ወሳኝነትና ቁርጠኝነት አለመኖር
- የአመራር አካላትና ባለሙያዎች በየጊዜው መቀያየርና መልቀቅ
- የተጠናከረ የህዝብ ግንኙነትና ፡የመረጃ ስርአት አለመዳበር
- በየደረጃው ያለው አመራር በደራሽ ስራዎች መጠመድ
- ለመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ሁሉም ሙሉ በሙሉ ለመተባበር ዝግጁ አለመሆን

# 7. *የክትትል ሪፖርትና የመገምገሚያ ስርአት*

በአዎንታዊ ታሳቢነት ተለይተው የተቀመጡ ዋና ዋና ጉዳዮች እነደተጠበቁ ሆኖ ጽ/ቤቱ እቅዱን በተጠበቀ ሁኔታ ለመፈጸምና የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ብሎም ተልኮውን ለመወጣት የሚያስችል ሁኔታ ድጋፋዊ ክትትል የግምገማ ስረአት ነድፎ ሲንቀሳቀስ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተሉትን የክትትልና መገምገሚያ ስርአት እንዲኖረ ተደርጓል፡፡

## 7.1. የክትትልና ሪፖርት ስርአት

የክትትልን ተግባር በተጠያቂነት የእቅዱን አፈጻጸም በምን ያህል መጠን በምን ያህል ጊዜ ፍጥነት በምን ያህል ጥራት ደረጃና በምን ያህል ወጪ ወይም በአጠቃላይ እቅዱ ለተተገበረበት በታሰበባቸው መስፈርቶችና የወጤት አመልካቾች መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ከተገቢው ምንም መረጃ የሚሰበሰብበትና የሚተነተንበት ሂደት ነው፡፡ በተጨማሪም በክትትሉ ሂደት ተለይተው የወጡ ደካመንቶችና ጠንካራ ጎኖችና በቀጣይ የእቅዱን ክንውን ወቅት ግብአት

በመሆን ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችል እና ግምገማ በሚካሄድበት ወቅት በመረጃነት የሚያገለግል ነው፡፡የክትትል ስራ በስራ ሂደት አስተሳሰብ በተቀረጸው መሰረት ስራዎችን በተቀመጠላቸው እስታንዳርድ መሰረት እየተከወኑ ስለመሆናቸው በስራ ሂደት አስተባባሪዎች ቢያንስ በየሁለት ሳምንቱ ክትትክ ሊካሄድ ይገባል ፡፡ከዚህ አኳያ የምንከተላቸው የክትትል ስርአቶች/ ስልቶች

1.ወቅታዊ ሪፖርቶችና መረጃዎች የክትትል ስርአቶች/ስልቶች

2. የሚከናወኑትን የትኩረት መስኮች በየጊዜው ቴክኒካል ድጋፍ ማድረግ

በአጠቃላይ ከቀረቡት ሪፖርቲችና ከሚሰበሰቡት የተገልጋይና የሰራተና አስተያየቶች መነሻ ሰፊና ተገቢ መድረኮችን ለማዘጋጀት መወያየትና በስራው ሂደት የተከሰቱ ቁልፍ ችግሮችን መንስኤ በመለየት የመፍቴ ሀሳቦችን ማውጣትና ለቀጣዩ የእቅድ አፈጻጸም ያለውን ጠቀሚታ መወሰንና ማስገንዘብ ያሻል፡፡

በእቅዱ አፈጻጸም በሚካሄዱ የክትትልና ግምገማ መሰረት ወቅታዊና ትክክለኛ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም  የሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት በወር፣በሶስት ወር፣በስድስት ወርና በአመት ውስጥ ሪፖርት የደረሳቸው አካላት ለተካሄደው አፈጻጸም ግብረ መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

## 7.2 **የግምገማ ስርአት**

የግምገማ ስርአት ውጤትና ስኬትን መለካት የሚያስችል የጊዜ ስፋት መከወን ስለሚገባው ቢያንስ በየሶስት ወር አንድ ጊዜ መከወን ያለበት ነው፡፡ ግምገማ በእቅድ ውስጥ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ በክትትል የተገኙ ወጤቶችን መሰረት በማድረግ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ ይህም እቅዱን በጊዜ ገደብ ለመስራት ከታቀደው ምን ያህል ውጤትና በምን ያህል ጥራት እንደተተገበረ ካጋጠሙ ችግሮችና መልካም ገጠመኞች አንጻር የሚገመገምበት ነው፡፡
በአጠቃላይ የክትትልና የግምገም ስርአት በተከታታይ የሚከወን ሆኖ የሚመለከታቸውን አካላት በተሟላ ሁኔታ ያሳተፈና የመረጃው አሰባሰብ ከተለያዩ አካላት ተወስዶ የተነጻጸረና በተገቢው ሁኔታ የተጣራ መሆን ይገባዋል፡፡ ክትትሉም ሆነ ግምገማው ሲካሄድ ከተዘረዘሩት ውጤት ስኬት ፋይዳ ወይም ለውጥ አመልካቾች ለግቡ መፈጸም ከሚያደርጉት አስተዋጽኦ አንጻር መሆን ይገባዋል፡፡

2002 REPORT (DOWLOADS)

# የ2002 1ኛ አጋማሽ የአምስት ወራት የስራ ሪፖርት

## የመሠራታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ በተመለካተ

የመሠራታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ በ2 ዙሮች ማለትም በመጀመሪያ ዙር 7 ሴክተር መስሪያ ቤቶች እንድሁም በ2ኛ ዙር 8 ሴክተር መስሪያ ቤቶች ሙሉ ትግበራ ለመግባት የሚያስችል ምደባ እና ስልጠና ለባለሙያዎች በመስጠት ትግበራው የተሳካ እንድሆን የድጋፊና ክትትል ስራ በያንዳንዱ ጽ/ቤት በሳምንት አንድ ቀን ለማድረግ ታቅዶ በአማካይ በ15 ቀን አንድ ግዜ ተደርጓል ። ሴክተሮች አገልግሎት አሰጣጣቸው የተቀላጠፈ እና ደንበኛ ተኮር እንድሆን በሁለቱ ዙር ትግባራ ለጀመረ ሴክተሮች ሁለት የተለያየ ዓይነት የመከታታያ ቼክ ሊስት ተዘገጅቶ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን የማለየት እና በደረጃ የማስቀመጥ ስራ ተሰርቷል ።

የተደረገውን የድጋፊና ክትትል ሪፖርት መነሻ በማድረግ የልዩ ወረዳው አስተባበሪ ኮሚቴ በ7ቱ ሴክተሮች ጉብኝት እንዲያደረግ ተደርጓል ። አስተባባሪ ኮሚቴው ከተደረገው ኢንስፔክሽን መነሻ የሁሉም ጽ/ቤት ኃላፊዎች ምክትል ኃላፊዎች እና አስተባበሪዎች በተገኙበት የአንድ ቀን የግብረ መልስ ውይይት ተደርጓል ።

የሠው ሀብት ስራ አመራር መመሪያን መነሻ በማድረግ ለድጋፊ የስራ ሂደቱ ፈፃሚዎች የአንድ ቀን ስልጠና ተሰጥቷል ።

ለመሠራታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ሙሉ ትግባራ ለኬት በጀት አስፈለጊ በመሆኑ ለሴክተር መስሪያ ቤቶች የሚመደቡ በጀቶች ተግበራውን ሊያሳካ በሚችል መልኩ ግብዓት ማሚለት አስፈለጊ በመሆኑ ለዚህ ትኩረት እንዲሰጥ የማስገንዘብ ስራ ተሰርቷል ።

ትግባራው የተሳካ እንዲሆን የአመራረ ቁርጠኝነት ወሳኝ በመሆኑ የመሠራታዊ የስራ ሂደት ለውጥ በካቢኒ ስብሳባ አጀንዳ በማስያዝ ውይይቶች እንዲደረጉ ተደርጓል ።

በድልድል ያልተካተቱ ሠራተኞች በተዘጋጁ አማራጭ መፍትሄዎች እንዲስተናገዱ ለማድረግ ከየሴክተረ መረጃ እየተደረጃ ይገኛል።

የፍትህ ሴክተር አመራሮች ፈፃሚዎችና የስራ ሂደት አስተባባሪዎች እስከ ቀበሌ መዋቅር ድረስ ቅንጅታዊ አሠራርን ማዳበር አስፈላጊነቱ ላይ የአንድ ቀን የፓናል ውይይት ተካሄዷል ፡፡

ጥረ አፈፃፀም ያላቸው ጽ/ቤቶችን የመለየት ስራ ተሰርቷል ፡፡ በየወቅቱ ከክልል የሚላኩ የ /BPR/ ደንቦችና መመሪያዎችን ጉዳዩ ለሚመለካታቸው ሴክተሮች የመላክ ስራ ተሰርቷል ፡፡

## የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን በተመለከተ

ህዝቡን አሣምኖ ማስራት የልማት ለውጥና ዕድገት እንዳሚያወጣ የገጠር ቀበሌ አመራረ ግንዘቤ እንዲኖረው በሁሉም ቀበሌያት የድጋፌና ክትትል ስራዎች ከአንድ ግዜ በላይ ተከናውነው በዚህም እየመጡ ያሉ ለውጦችን የመከታተል ስራዎች እየተከነወኑ ይገኛሉ ፡፡

ህዝቡ በጋራ በግል ስራ የሚሳተፉበትን ሠዓት ወስኖ መንቀሳቀስ እንዳለበት በየቀበሌው በሚደረጉ ድጋፌና ክትትል የማስገነዘብ ስራ ተሰርቷል ፡፡

ከ39 ቀበሌያት አስር አስር ሞዴል በአጠቃላይ በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ መሠረተ ተመልምሏል ፡፡

በቀበሌ የሚሰረ ስራዎች ህዝቡን ያማከሉ እንድሆኑ ለማድረግ ከዕቅድ ዝግጅት እስከ ክትትልና ግምገማ ድረስ ህዝቡ እንዲሳተፌ በማድረግ ተጨባጭ የልማትና የመልካም አስተዳደር ለውጦች እንዲመጡ እየተደረገ ይገኘል ፡፡

በቀበሌ ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ ገቢዎችና የሚወጡ ወጪዎችን ህዝቡ እና አመራረ እንዲያወቃቸው ያስችል ዘንድ የተለያዩ ቅጾችን ለአመራረና ስራ አስከያጁ የአንድ ቀን ስልጠና በመስጠተ ተሰራጭቷል ፡፡

ቶሎ ምላሽ ከመስጠተ አንፃር እየታዩ ያሉ ለውጦችን ለመለካት የድጋፌና ክትትል ስራዎች በወረዳ እና በቀበሌ የመንግስት ተቋማት ተከናውኗል ፡፡

አመራረ እና የቀበሌ ስራ አስኪያጅ በጋራ ጉዳዩችን ቶሎ መፍታት እንዳለባቸው እና ባለጉዳይ ለአስፈለጊ የግዜ የገንዘብ እና የጉልበት ወጪ ህዝቡ እንድያወጣ የግንዘቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡

በለጉዳይ የሚባዛበቸው አስር የልዩ ወረዳው የገጠር ቀበሌያት የመለየት ስራ ተሠርቷል ፡፡ፌትሃዊነት እና የህግ የባለይነት እንዲሰፍን በልዩ ወረዳው የሚሰረ የልማት ስራዎች በፍትሃዊነት የህዝቡን ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥ በሚችል መልኩ እንዲሆን ጥረት እየተደረገ ይገኛል ፡፡

አገልግሎት አሰጣጦች ፍትሃዊ በሆነ መልኩ እንዲከናወኑ የባለጉዳይ  ወረፋ መጠበቂያ ካርዶች በወረዳ እና በቀበሌ የመንግስት መስሪያ ቤቶች አገልግሎት እንዲሰጡ ጅምር ስራዎች ተካናውኗል ፡፡

በአገልግሎት አሳጣጥ በመረጃ አያያዝ በፋይል አደረጃጀት የአመራረን እና የቀበሌ የልማት ስራዎችን ከመደጋፌ እና ከመሳሰሉት አንፃር የቀበሌ ስራ አስከያጆች እያከናወኑ ያሉትን ስራ ለማደገፍ በቼክ ሊስት የኢንስፔክሽን ስራ በ79 ቀበሌያት ተከናውኗል ፡፡

በዚህም በደረጃ የመለየት ስራ ተሰርቷል ::በገጠር ቀበሌያት የኮሚኒቲ ፓሊሲንግ ማቋቋም አስፈለጊነት ላይ ከፍትህ ሴክተር አካላት ጋር የጋራ መግባባት በመፍጠር የማህበረሳብ ፓሊሶች በየቀበሌው እንዲቋቋም ተደርጓል ::

የኮሚፒተር የፕሪንተር ጥገና የሶፍትዌር ኢንስታሌሽን የአንቲ ቫይረስ ኢንስታሌሽን የላን ትን ኮምፒተሮች ኦፕሬቲንግ ሲስተም አፕግሬድንግ የፕሪንተር ኢንስታሌሽን በልዩ ወረዳው ስምንት ጽ/ቤቶች ተከናውኗል ::

የ IT ድጋፌና ክትትል የኢንተርኔትና መሠረታዊ ኮምፒተር ስልጠና በታቀደው መሰረት ለ 1 ሳምንት ተከናውኗል ::

የኢንተርኔት አጠቃቀም ለኃላፊዎችና ምክትል ኃላፊዎች ለመስጠት የማኑዋል ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል ::